አብይ በቆፈረው ጉርጓድ ይቀበራል። 'ደባ ራሱን፣ስለት ድጉሱን' ንውና (ይማሙ ይመር፣ ሃኪም)

በአማራው ሁለንተና የሚቀኑት፣ አማራ ያለመሆናቸው፣ የሚያብከነክናቸው ወያኔና መናጆ ኦሮሞዎች፣ ስልጣን ቢጨብጡም ፣ ከእኩይ ማንናታቸው አልተላቀቁም። አገር ሲታደግ የኖረውን አማራ፣ ሲያሳድዱት፣ ሃይ ባይ ስላላጋጠማቸው የልብልብ በቃቸው። ወያኔ ትግሬ ዘነጣጥሎ ያስቀራትንም የኢትዮጵያ፣ ጠቅልለው ኦሮምያ ሊሏት፣ የተጣደፉ ይመስላል።

ወያኔዎች በፋሽስት ጣልያን የተገዙ ባንዳ ዝርዮች ናቸው። እነርሱና እና ምንደኛው አነግ፣ ላለፉት 30 ዘመናት ባማራው የግፍ ግፍ ቢፈፅሙም ፣ አማራው የነቃው ገና ትላንት ነው። ቁጣው አልጎመራም ። ለኢትዮጵያ አንድነት ሲል ሲለበለብ ፣ ደብዛው ሊጠፋ የደረሰ እስኪመስል የተገፋው አማራ ፣ የተደናገረ ቢመስል፣ ሊዳፈን የማይችል የእሳት አለሎ መሆኑን ባላንጦቹ አልተረዱም።

" ከሳ ጠቆረ ፣ ብለው ቢደፍሩት፣

ያመረረ እለት፣ አይማለዱት "ይላል አማራ ሲቆጣ።

አብይ በህዝብ አመፅ፣ መሪ ቢሆንም ፣ ገና ሰው አልሆነም። ፍጡር ከባህርዩ በላይ ስለማይውል። በአብዮት አደባባይ ከህዝብ ሊተዋወቅ ብቅ እንዳለ ቦምብ ፈንድቶ ሰዎች ሲጎዱ፣ ግብዝ ለመሆኑ ፍንጭ ሰጥቶ ነበር። " እኔ ብጎዳ ኖሮ፣ የቡራዩ/የሱልልታ ፈረሰኞች መጥተው ቀውስ ይፈጠር ነበር' ማለቱ፣ ያሞካሸውን መንጋ ማስቀየሙ፣ አላሳሰበውም።

የግፍ ተግባራቸው እንደሚያባንናቸው ወያኔ አለቆቹ፣ ይህ ሰው ከሰላይ አጋሩ ለማ ጋር፣ በተለይ በአማራው፣ በፈፅመው ግፍ ፣ ተርበትብቷል። ስለዚህ፣ አማራውን፣ ጅራቱን እንደተያዘ ነብር ይፈራዋል። የሚከተሉትን ለዋቢነት እንመልከት፣

1) ብሶት የወለደውን የአማራ ምሁራን ድርጅት ገና እንደተቋቋመ ነበር፣ ሰላዩን አብይን ብርክ የመታው፣
2) እልቆ መሳፍርት የሌላቸው ያልታጠቁ አማሮችና ሌሎች፣ በወራሪ ኦሮሞዎች ሲጨፈጨፉ፣ አዲስ አበባ ዙርያም፣ ቤታቸው በቁማቸው ሲፈርስባቸው፣'አልሰማሁም' ያለው፣
3) ኢትዮጵያን የወረሩት ወያኔና የአነግ ህገ-መንግስት፣ ፀረ-አማራ ስለሆነ መሻሻል አለበት ያሉትን ከመገሰፅ አልፎ፣ በታላቁ የአማራ ህዝብ ለመሳለቅ የሞከረው፣
4) ወያኔና ፣ አነግ ፣ የአማራን አፅመርስት ተቀራምተው የከለሉትን መሬት ጉዳይ፣ለይስሙላ ሽምግልና ፣ ቅርምቱን ያኪዩሄዱትን ወንጀለኞች ጭምር ፣ በአጣሪነት መሰየሙ፣
5) ከአዲስ አበባ ነዋሪዎች ከመቶው 60 አማሮች ፣ 25 ደግሞ ሌሎች አማርኛ ተናጋሪዎች ናቸው። ግን ለከተማዋ ፍፁም እንግዳ የሆንን ኦሮሞ፣ ደንብ ሽሮ መሾሙና ለውደፊትም፣ ያሻውን ኦሮሞ ለመሳለት መዛቱ፣
6) በሰበብ አስባብ የአማራን ልሂቃን ፣ እነ **ክርስቲያን ታደለን፣ በለጠ ካሳን፣** ከደፍን ኢትዮጵያ እያፈነ ሲያስር፣ የኦሮሞ ነፍሰ-ገዳዮች፣ ከሃያ በላይ ባንኮች የዘረፉን፣ ኢትዮጵያውያንን በገፍና በግፍ ያስፈጁ አሸባሪዎች፣ በኢትዮጵያ ህዝብ ሃብት እንዲምነሸነሹ ማድረጉ፣
7) ደሴ ሄዶ፣ አንድ ምዕመን ቤትክርስቲያናትን ከመቃጠል መታደግ የመንግስት ድርሻ መሆኑን ሊያዝነዝቡት ቢሞክሩ፣ በዕብሪት " ቃጠሎው ሊቀጥል ይችላል፣ ብሎ ታዳሚን ሁሉ ማስደንገጡ፣
8) ኦሮምያ ተብሎ፣ በተወረረውና 30 ሚሊየን በላይ ነባር ኢትዮጵያዊያን በሚሰቃዩበት ክልል፣ አምስት ሺህ በላይ በሆኑ አማራ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ፣ የሚፈፀመባቸውን እጅግ አሰቃቂ ድርጊት በቸልታ ማየቱ
9) ለዘመናት በታላቅ ድካም የተመሰረተውን የኢትዮጵያ ሰራዊት፣ በሴራ በታትኖ የወራሪ ትግሬ መፈንጫ ያደረገው አነግ ፣ ዛሬ አቢይ የኢትዮጵያን ሰራዊት ፣ በተገንጣይ ኦሮሞዎች መተካቱ፣
10) ያገሪቷን ዋልታና ምሰሶ የነበረ አማራ፣ ከአመራር አብርሮ፣ በዘውግኛ ኦሮሞዎች መተካቱ፣ የዘር ፍጅቱ አካል ነው። አማራውን ለመውጋት፣ በሺዎች ኦሮሞ ጦር፣ አሰልጥኖ ለወረራ ማቆብቆቡ፣

በመጨረሻ የአቢይና ለማ፣ ሰው የመሰላችሁት ህዝብ፣ በንቀት 'ድመት መንኩሳ፣ አመሏን አትረሳ' ይላችኋል። በምትቆፍሩት ጉርጓድ ከመቀበራችሁ በፊት፣ አምላካችሁ፣ ልብም አዕምሮም እንዲቸራችው እየተመኘሁ አንድ ቃል ልበል። **በግፍ ያሰሯችኋቸውን አማሮች፣ እነ ክርስትያንን ባስቸኳይ ፍቱ።** ከእንቧዩዋ (**በኦሮምኛ፣ ሂዲ**) ተማሩ። እንቧይ ስትጎን (አየር ላይ ስትውረገረግ) ፣ መፍረጧን አትገነዘብምና። አይናቸውን የገለጡ ዕለት፣ የገዛ አሮሞ ወገኖቻችሁ፣ ባስፈፅማችኋቸው ወንጀሎች፣ ባስከተላችሁባቸው ጥላቻ፣ ድንቁርና፣ ድህነት፣ እርዛት ፣ ስደት፣ ውርደት፣ ይፋረዷችኋል። አይቀርም። የፋሽስቱን መሪ ሙሶሎኒን፣ ቁልቁል የሰቀሉት፣ ወገኖቹ እንደነበሩ ልብ ይሏል።